ቁጥር አብክመ ገ/ቢ/ሃ/ሪ-01/02

ቀን 15/09/2014 ዓ/ም

ለ 91 ቢሮ/ጽ/ቤት/ኤጀንሲ/ባለስልጣን/ኮሚሽን/ኢንስቲትዩት
ባ/ዳር

ለ 19 ዞን/ሜትሮፖሊታንት ከተማ/አስ/ገን/ኢኮ/ትብ/መምሪያ

ጉዳዩ፡- በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ የተደረገ ማሻሻያን ስለማሳወቅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ በሥራ ላይ ያለውን የግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር መመሪያ የማሻሻል በአዋጅ ቁጥር 179/2003 አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 47 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የመንግስት፡-

1. ግዥ አፈፃፀም የገንዘብ ጣሪያ /Threshold/፣
2. የንብረት አወጋገድ አፈፃፀም ፣
3. በመንግስት የግንባታ ግዥ ላይ የሚያጋጥሙ የአፈፃፀም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል

የመመሪያ ማሻሻያ አውጥቷል።

በመሆኑም የተሻሻለውን መመሪያ 8 ገጽ በዚህ ደብዳቤ ሽኝነት የላክንላችሁ ስለሆነ ከግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንድታውሉ እያሳወቅን የዞን/የከተማ/አስ/ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያዎች በስራችሁ ለሚገኙ የወረዳ/የከተማ/አስተዳደር ገ/ጽ/ቤትና ለክልል ተጠሪ መ/ቤቶች ተደራሽ እንድታደርጉ እናሳስባለን ።

የቢሮው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዳይሬክቶሬትም የመመሪያ ማሻሻያውን በቢሮው ድህረ-ገጽ ላይ በመጫን ለሚመለከታቸው የመመሪያው ተጠቃሚ አካላት ተደራሽ እንዲያደርግ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲደርሰው ተደርጓል።

"ከሠላምታ ጋር"

ጎላሁን መኮሪ አንተነህ(ዶ/ር)
ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ//

- ለም/ቢሮ ኃላፊ /በጀት ዘርፍ/
- " " /ፋይናንስ ዘርፍ/
- ለግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለመ/ግ/ን/አ/አ/ክ/ዳይሬክቶሬት
- ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዳይሬክቶሬት

ገንዘብ ቢሮ

መግቢያ

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትኃዊ እና አድሎዎ የሌለበት እንዲሁም ውጤታማ እና ለግዥ የሚውለዉ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ፋይዳ ማግኘት በሚያስችል መልኩ ሥራ ላይ እንዲዉል ማድረግ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 እና የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2003 ዋና ዓላማ ነው።

ይሁን እንጅ ዘርፉ በባህሪዉ ተለዋዋጭ (Daynamic) ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በሃገር ደረጃ እየታየ ያለዉ የብር የምንዛሪ ለዉጥ እና ተያያዥ የገበያ ሁኔታዎች በግዥ አፈፃጸም እና ንብረት አወጋገድ ተግባራት ብሎም በመንግስት መ/ቤቶች ዋና ዋና የልማት ግቦች ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል።

በመሆኑም የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ለአፈፃጸም የበለጠ አመቺና ቀላል፤እንዲሁም ዉጤታማ እና ለመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ፋይዳ በሚያስገኝ መንገድ ለመተግበር ይቻል ዘንድ ከዚህ በታች በተመለከቱት በአፈፃጸም ላይ በሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ዙሪያ የአሰራር ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ከዚህ በታች የሚከተለዉን ማሻሻያ በሥራ ላይ አዉሏል።

1- አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በግዥ እና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ላይ የተደረገ ማሻሻያ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2- ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 አንቀጽ 62 ንኡስ አንቀጽ 2 እና በግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 47 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ ይህን የመመሪያ ማሻሻያ አዉጥቷል።

ክፍል አንድ

3- ግዥ ለመፈጸም የተፈቀደ የገንዘብ ጣሪያን/Threshold/፡-

ባለፉት ዓመታት በብሄራዊ ደረጃ የተደረገውን የብር የምንዛሪ ማሻሻያ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ በገበያው ላይ የተፈጠረውን የዋጋ ንረት እንዲሁም በሀገር ደረጃ የውጭ የምንዛሪ እጥረት በግዥ አፈፃጸሙ ላይ እያሳደረ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስቀረት እና የሀገር ውስጥ አቅራቢዎችን ለማበረታታት ሲባል በሥራ ላይ ያለውን ዓለም አቀፍ ግዥ የገንዘብ ጣሪያ ላይ የሚከተለዉ ማሻሻያ ተደርጓል።

3.1. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ

በግዥ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከቱት በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈጸም የሚገባው የግዥው የገንዘብ መጠን ከሚከተለው በላይ ሲሆን ነው ።

3.1.1- ለግንባታ ስራ በስራ ላይ ያለው ብር 150,000,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 1,500,000,000፤

3.1.2- ለዕቃ ግዥበስራ ላይ ያለው ብር 50,000,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር1,000,000,000፤

3.1.3- ለምክር አገልግሎት በስራ ላይ ያለው ብር 7,500,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 100,000,000

3.1.4- የምክር ያልሆነ አገልግሎት ግዥ በስራ ላይ ያለው ብር 21,000,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 150,000,000 ሆኗል።

3.2. <u>ውስን ጨረታ፡-</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 17 ንኡስ አንቀጽ 3.1 በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈጸም የገንዘብ ጣሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

3.2.1- የግንባታሥራ ግዥበስራ ላይ ያለው ብር 6,000,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 20,000,000፤

3.2.2- የዕቃ ግዥ በስራ ላይ ያለው ብር 1,500,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 5,000,000፤

3.2.3- የምክር አገልግሎት ግዥ በስራ ላይ ያለው ብር 900,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 2,250,000፤

3.2.4- ምክር ያልሆነ አገልግሎት ግዥ በስራ ላይ ያለው ብር 1,200,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 3,000,000 ሆኖ ተሻሽሏል።

3.3 <u>በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ፡</u>

በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ የምክር አገልግሎት ግዥ በስራ ላይ ያለው ብር 50,000 የነበረዉ የገንዘብ ጣሪያ ተሻሽሎ ብር 200,000 ሆኖ ተሻሽሏል።

ክፍል ሁለት

4. ለግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ አሰሪ መ/ቤቱ በትክክለኛ መረጃ ከተዘጋጀ የመሃንዲስ ዋጋ ግምት በታች የተጋነነ ዝቅተኛ ዋጋ እና ከፍተኛ ዋጋ ሞልተዉ አሸናፊ ሆነዉ የሚመረጡ ተቋራጮች ወይም ተጫራቾች፡

ሀ/ በመንግስት መ/ቤቶች የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ግዥ ላይ በጨረታ ግምገማ የሚመረጡ አሸናፊዎች የሞሉት ዋጋ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ በትክክለኛና ወቅታዊ የገበያ መረጃ በተዘጋጀ የመሃንዲስ የዋጋ ግምት ማለትም ቅኝትና መሰረተ ልማት ቢሮና ተዋረድ መምሪያዎች በየሩብ ዓመቱ የሚያዘጋጁትን የዋጋ ጥናት በመጠቀም ከዚህ ጥናት ውጭ ሲሆኑ ፤ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ

ኤጀንሲ፤ ከንግድና ገበያ ልማት ተቋማት፤ ከአምራች ድርጅቶች፤ ከአከፋፋዮች እና ከእነዚህ አማራጮች ካልተገኘ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቋቋም የገበያ ጥናት ኮሚቴ በሚቀርብ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ ላይ ተመስርቶና በቃለ-ጉባኤ ተደግፎ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የጸደቀ መረጃ በመያዝ ከተዘጋጀዉ የመሃንዲስ ዋጋ ግምት አንፃር የተጋነነ ዝቅተኛ ከ25% ዝቅ ብሎ በመግባቱ ተጫራቹ በተፈለገዉ ጥራት እና ጊዜ ማከናወን አይችልም ብሎ አሰሪ መ/ቤቱ ሲያምን፦

1) በጨረታዉ የተጋነነ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበዉ ድርጅት ወይም ተቋራጭ ዝርዝር የግንባታ ዋጋ (Cost Breakdown) እና የግንባታ መርሃ-ግብር (Project Work Schedule) እንዲሁም ባቀረበዉ የተጋነነ ዝቅተኛ ዋጋ መስራት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ (Conformation Letter) አሸናፊነቱ በተገለጸ በ5 የሥራ ቀናት ዉስጥ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህን ማድረግ ካልቻለ ከዉድድር ዉጭ ሆኖ ሁለተኛ የወጣዉ ተጫራች የሞላዉ ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃጸር የተሻለ ሆኖ ከተገኘ ሥራዉ ለዚሁ ተወዳዳሪ የሚሠጥ ይሆናል።

የሚቀርበዉ ዝርዝር የግንባታ ዋጋ (Cost Breakdown) አሰሪዉ መ/ቤት ተጫራቹ የሞላዉን ዋጋ ከወቅታዊ የፋብሪካ ዉጤቶች ወይም የግንባታ ግብዓቶች የገበያ ዋጋ ጋር በማነፃጸር ለመወሰን የሚያስችለዉ ይሆናል።

2) የተጋነነ ዝቅተኛ ዋጋ ሞልተዉ አሸናፊ ሆነዉ የሚመረጡ የግንባታ ተቋራጮች ዉል ይዘዉ ወደ ሥራ ሲገቡ የቅድሚያ ክፍያ አይፈቀድላቸዉም።

3) የሚያስይዙት የዉል ማስከበሪያ በግዥ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 14.20 ንኡስ አንቀጽ 3 ሥር ከተፈቀዱ የውል ማስከበሪያ ዓይነቶች ማለትም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና፤ CPO፤ ጥሬ ገንዘብ ሆኖ የሚሰላበት የገንዘብ መጠን የጨረታ አሸናፊዉ የሞላውን ጠቅላላ ዋጋ 10% የነበረዉ ተሻሽሎ 25% የዉል ማስከበሪያ ዋስትና ማስያዝ ግዴታ ይሆናል።

ለ/ በመንግስት መ/ቤቶች በሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክት ግዥዎች ላይ በጨረታ ግምገማ የሚመረጡ አሸናፊዎች የሞሉት ዋጋ አሰሪ መ/ቤቱ በትክክለኛና ወቅታዊ የገበያ መረጃ ተመስርቶ ከተዘጋጀዉ የመሃንዲስ የዋጋ ግምት በላይ እስከ 10% ድረስ ከፍ ብሎ ዋጋ ሞልቶ ከቀረበ አሰሪ መ/ቤቱ ድጋሚ ጨረታ ቢወጣ የሚወስደዉን ጊዜና የወቅቱን የገበያ ተለዋዋጭነት ግምት ዉስጥ በማስገባት አዋጭ ነዉ ብሎ ያመነበትን በመወሰን የመንግስትን ጥቅም ሊያስጠብቅ በሚችል መልኩ ግዥዉን መፈጸም ይችላል።

ሐ/ በግንባታ ግዥ አፈፃጸም ወቅት ተጫራቾች በዉድድር ሲሳተፉ የግንባታዉን የመጫረቻ ዋጋ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ካሉ የሥራ ዝርዝሮች ከመሃዲስ የዋጋ ግምት አንፃር ከ25% በላይ የተጋነነ ዋጋ ስለመሙላታቸዉ ሲረጋገጥ፤-

1) የክፍያ አፈፃፀሙ በአማካሪ መሃንዲሱና በአሰሪ መ/ቤቱ በትክክለኛ የዋጋ መረጃ በተዘጋጀዉ የመሃንዲስ የዋጋ ግምት መሰረት በየክፍያ ሰነዱ ከ25% በላይ ያለውን የገንዘብ መጠን እየቀነሱ

በማስቀረት የግንባታዉ አጠቃላይ ሥራ (Phisical Progres) 100% እንደተጠናቀቀ ከመጨረሻዉ ዙር ክፍያ ጋር ተደምሮ የሚከፈል ይሆናል።

2) በግንባታ ግዥ ላይ የዋጋ አሞላሉ በአጠቃይ ሲታይ ለጀኔሬተር፤ የግቢ ዉስጥ የአስፋልት ሥራ፤ የኤሌክቶሮ መካኒካል ሥራዎች እና የመሳሰሉት ላይ ያሉ የነጠላ ዋጋ አሞላላቸዉ ከምህድስና ግምት አንፃር ሲታይ ከ25% በታች ሆኖ ከተገኘ ከገበያ ጥናቱ በልጦ በእነዚህ ሥራዎች የሚታየዉን የገንዘብ መጠን በየደረጃዉ ከሚፈጸም ክፍያ ቀንሶ በማስቀረት ሥራዎች ሲጠናቀቁ ከመጨረሻ ክፍያዎች ጋር ተደምሮ የሚከፈል ይሆናል።

3) የግንባታ ሥራ ክፍያ አፈፃጸሙ የአሰሪ መ/ቤቱ አማካሪ መሃንዲስ በሚያቀርበው የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት ሆኖ የተሰራዉ የግንባታ መጠንና በዉሉ መሰረት ሊከፈል ከሚገባዉ ገንዘብ ጋር ተገናዝቦ (Phisical & Financial Progres) ምጥጥን Ratio) አግባብነት እየተረጋገጠ የመጀመሪያ የክፍያ ጥያቄ መቅረብ የሚችለዉ ፦

- እስከ ብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን) ለሚያወጣ የግንባታ ግዥ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ሥራ ቢያንስ 5% እና ከዚያ በላይ እንዳጠናቀቀ እና፡-
- ከብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን) በላይ ለሚያወጣ የግንባታ ፕሮጅክት ደግሞ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ሥራ ቢያንስ 2.5% እና ከዚያ በላይ መጠናቀቁ ሲረጋገጥ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል።

መ/ በግዥ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 29.2 የግንባታ ዘርፍ ስራዎች የክፍያ የምስክር ወረቀት አፈፃጸም በተመለከተ፡-

1) በንኡስ አንቀጽ 2 አማካሪ መሃንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ7 (ሰባት) ቀናት ዉስጥ የጥያቄዉን አግባብነት አረጋግጦ ማጠናቀቅ አለበት። ሆኖም አማካሪ መሃንዲሱ በ7 (ሰባት) ቀናት የጊዜ ገደብ ዉስጥ አጠናቆ ባለማቅረቡ በተቋራጩ ላይ ለሚደርሰዉ የክፍያ መዘግየት ለጉዳት ማካካሻ በክፍያ የምስክር ወረቀቱ እንዲከፈል የታመነበትን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማበደሪያ የወለድ ምጣኔ የሚገኘዉን የገንዘብ መጠን ለሥራ ተቋራጩ የመክፈል ግዴታ አለበት።

2) በንኡስ አንቀጽ 3 የክፍያ ምስክር ወረቀት በአማካሪ መሃንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ የመንግስት መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለስራ ተቋራጩ መፈጸም አለበት የሚለዉ ተሻሽሎ በቀረበ በ15 (በአስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የመንግስት መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለስራ ተቋራጩ መፈጸም አለበት በሚል ተሻሽሏል።

ዉል ሰጭ የመንግስት መ/ቤት ክፍያዉን መፈጸም የሚያስችል በጀት እያለዉ የክፍያ ጥያቄዉ በቀረበ በ15 (የአስራ አምስት) የሥራ ቀናት ዉስጥ ለሥራ ተቋራጩ ክፍያ ባይፈጽም በተቋራጩ ላይ በክፍያ መዘግየት ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ካዘገየበት ቀን ብዛት በክፍያ የምስክር ወረቀቱ

የገንዘብ መጠን መሰረት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማበደሪያ የወለድ ምጣኔ ለሥራ ተቋራጩ ጉዳት ማካካሻ የመክፈል ግዴታ አለበት።

በዚህ መንገድ የተከፈለዉ የገንዘብ ወጪ በፍታብሄር ህጉ መሰረት በወቅቱ ሥራን በአግባቡ ካልመራዉ የሥራ ኃላፊ ወይም ደመወዝ ላይ እየተቀነሰ ለመ/ቤቱ መተካት ይኖርበታል።

ሠ/ የተጨማሪ (Additional) ግንባታዎች እና የለዉጥ ሥራ (Variation) በተመለከተ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀጽ 19 ተራ ቁጥር 2 ንዑስ ቁጥር 2.3 እና አንቀጽ 29.2 በተራ ቁጥር 4 ላይ የተቀመጡት የአፈፃፀም ስልቶች እስከነማሻሻያዎች በሚከተለው ተተክተዋል፦

1) በመንገድ ግንባታ፣ በንጹህ መጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና በመስኖ ግድብ ሥራዎች ላይ የሚፈጠር የተጨማሪ (Additional) ግንባታዎች እና የለዉጥ ሥራ (Variation) የቀረበዉ ጥያቄ ሲታመንበት በአንድ የግንባታ ፕሮጀክት ዉል ከመጀመሪያ አጠቃላይ ስምምነት ከተደረሰበት የግንባታ ዋጋ የሁለቱ ድምር እስከ 50% ድረስ ብቻ ተፈቅዷል።
2) በህንፃ እና ተያያዥ ግንባታዎች ላይ የሚፈጠር የተጨማሪ (Additional) ግንባታዎች እና የለዉጥ ሥራ (Variation) በአንድ የግንባታ ፕሮጀክት ዉል ከመጀመሪያ አጠቃላይ ስምምነት ከተደረሰበት የግንባታ ዋጋ የሁለቱ ድምር እስከ 30% ድረስ ብቻ በሚል ተተክቷል።

ሆኖም ግን ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጹት የተጨማሪ (Additional) ግንባታዎች የሚፈቀዱት የለውጥ ሥራ (Variation) አለመኖሩ ከተረጋገጠ እና የለውጥ ሥራ (Variation) ካለ መጠኑ ከተፈቀደዉ በላይ ካልሆነ ብቻ ይሆናል።

3) በአንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውል መሰረት ከተያዘውና በስምምነት ከተደረሰበት ውጭ የተጨማሪ (Additional) ግንባታዎች እና የለዉጥ ሥራ (Variation) ለሚጠይቅ የገንዘብና የጊዜ መጠን ለተጨማሪ እና ለለዉጥ ሥራ እስከ 10% አሰሪ መ/ቤቱ ከአማካሪ መሃንዲስ ጋር በመመካከር በቅድሚያ ዉል ተይዞ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል። ሆኖም መጠኑ ከ10% በላይ እስከ 30% በሚሆንበት ጊዜ፦
   - በወረዳ አስተዳደር የሚፈፀሙ የግንባታ ግዥዎች በወረዳ የገንዘብ ጽ/ቤቶች እና የከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤቶች፤ የከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት በሌላቸው ወረዳዎች የዞኑ ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ በጋራ ይፈጸማል።
   - በክልል የሚፈጸሙ የግንባታ ግዥዎች በገንዘብ ቢሮ እና በከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ በጋራ በመመካከር ሲታመንበት የሚፈጸም ይሆናል።
4) በወረዳ አስተዳደር የሚፈፀሙ የግንባታ ግዥዎችን በተመለከተ ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአሰሪ መ/ቤቱ በሚቀርብ ጥያቄ ወይም በራሱ ዉሳኔ የክልል ቢሮዎቹ (ገንዘብ ቢሮ እና ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ) በልዩ ሁኔታ ሂደቱን የመመርመር ስልጣን አላቸው።

5) ተጨማሪ /Additional/ እና የለውጥ ሥራ /Variations/ ፈቃድ ጥያቄ ተፈፃሚ የሚሆነዉ የጥያቄዉ አግባብነት ለመወሰን ስልጣን በተሰጠዉ አካል ሲታመንበት ብቻ ይሆናል።

ይህም ማለት ጥያቄዉ የከተማና መሰረተ ልማት ቢሮና ተዋረድ ተቋሞች ማስረጃ ሲያቀርቡና ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ የሚፈቀድ ይሆናል።

ይህን ተግባር ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀት ያላቸዉ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች በራሳቸው መሃንዲስ ወይም አማካሪ በመቅጠር ያዘጋጁትን ዲዛይን እና የሥራ ዝርዝር በከተማና መሰረተ ልማት ቢሮና ተዋረድ መ/ቤቶች በማጸደቅ ወደ ሥራ መግባት ይኖርባቸዋል።

6) ከአቅም በላይ እና አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት በሚፈጠር የስራ ለዉጥ በአሰሪ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ ለሚፈጠረዉ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ ዲዛይን የሚያዘጋጁና የሚያጸድቁ እንዲሁም አማካሪ ባለሙያዎች በክልሉ በሥራ ላይ ባሉ ልዩ ልዩ የሕግ ማዕቀፎች መሰረት ተጠያቂነት አለባቸዉ።

ረ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ ለመፈጸም የሚደረግ የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) ማስተካከያን በተመለከተ፡-

1) የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) በባለሙያ ወይም የኮሚቴ አባል በሆነዉ አማካሪ መሃንዲስ ማስተካከል የሚቻለው ጠቅላላ ዋጋን ብቻ ሲሆን አቅራቢዉ ከተጠቀመበት እስክርቢቶ በተለዩ ቀለም በአንድ መስመር " **ሰረዝ** " በማድረግ በአቅራቢው የተሞላውን ጠቅላላ ዋጋ ብቻ በማረም በሂሳብ ስሌት የተገኘዉን ትክክለኛ ዋጋ ማስቀመጥ አለበት።

2) ለፋይናንስ ግምገማ ያለፉት ተጫራቾች በቁጥር፤

- ቢያንስ 3 እና በላይ ከሆኑ በጨረታ አከፋፈት ወቅት ከተነበበዉ አጠቃላይ ዋጋ ላይ የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) ከተሰራ በኋላ የተደረሰበት ልዩነት እስከ 2.5% ድረስ ከሆነ ተቀባይነት የሚኖረዉ ሲሆን ከዚህ የበለጠ ልዩነት ካጋጠመ ከውድድር ውጭ ይሆናል።
- ከ3 በታች ከሆኑ በጨረታ አከፋፈት ወቅት ከተነበበዉ አጠቃላይ ዋጋ ላይ የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) ከተሰራ በኋላ የተደረሰበት ልዩነት እስከ 1% ድረስ ብቻ ተቀባይነት የሚኖረዉ ሲሆን ከዚህ በላይ ከሆነ ከውድድር ውጭ ይሆናል።

3) የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) በግዥ ፈፃሚዉ መ/ቤት ባለሙያ ከሚስተካከለዉ ዉጭ በተጫራቾች የሚቀርበዉ የመጫረቻ ሰነድ ላይ በነጠላ እና ጠቅላላ ዋጋ ላይ ስርዝ ድልዝ ካለ ተጫራቹ ከጨረታ ዉጭ ይሆናል።

4) የግዥ ሰነዶች በሚመለከታቸዉ ግዥ ባለሙያዎችና ግዥ ፈፃሚ የሥራ ክፍል ዉስጥ ብቻ በጥንቃቄ መያዝ አለባቸዉ።

5) ከላይ የተቀመጡት መመዘኛዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በቅድሚያ መመዘኛዉ በተጫራቾች መመሪያ ተካቶ ተጫራቾች እንዲያዉቁት መደረግ አለበት።

ሰ/ ይህ የመማሪያ ማሻሻያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተጀምረዉ ያልተጠናቀቁ የመንግስት የግንባታ ሥራዎች ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበረዉ አሰራር መሰረት እንዲጠናቀቁ ይደረጋል።

5- አማካሪ ድርጅቶችን ለመቅጠር የሚደረግ ስምምነት አንድን ፕሮጀክት ለማስጸም በሚያስችል አጠቃላይ የቁርጥ ዋጋ ሆኖ የአመካሪዉ ክፍያ አፈፃጸም የፕሮጀክቱን የአፈፃጸም ደረጃ (ፕሮግረስ) መሰረት በማድረግ የሚፈጸም ይሆናል።

በአማካሪ ድርጅቱ ባልሆነ ምክንያት ለሚፈጠር የሥራ መቋረጥ አማካሪ ድርጅቱ በፕሮጀክት ለመደባቸዉ ባለሙያዎች የ3 ወር ክፍያ በአሰሪዉ መ/ቤት በኩል ተፈጽሞ በቀጣይ ክፍያ የሚቋረጥ ይሆናል። ይሁን እንጅ፡-

- የአማካሪ ድርጅቱ ክፍያ በተቋረጠ 3 ወራት (ግንባታዉ በተቋረጠ በ6 ወራት) ዉስጥ ፕሮጀክቱ የሚጀምር ከሆነ ቀጣይ ሥራዉ በመጀመሪያው የውል ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።
- ፕሮጀክቱ ከዚህ በላይ ከዘገየ እና በአዲስ ዉል ለማስቀጠል ስምምንት ከተደረሰ እና የተሻለ ዋጋ አይገኝም ተብሎ ሲታመን የቀሪ ሥራዉን የዉል ዋጋ የመጀመሪያዉ ዉል መሰረት በማድረግ እስከ 10% ድረስ የዋጋ ጭማሪ ወይም ማስተካያ ዉል ተይዞ ወደ ስራ መግባት ተፈቅዷል።

6-ይህ የመመሪያ ማሻሻያ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተዉ በግልጽ ጨረታ በሚወዳደሩበት ወቅት በእነሱም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

7. <u>አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አወጋገድ፡-</u>

የመንግስት ተቋማት የማይጠቀሙባቸዉን ንብረቶች በወቅቱ ማስወገድ እንዲችሉ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 31 እና 42 ላይ የሚገኙ አንቀፆች ተሻሽለዉ የንብረት ማስወገድ የግንዘብ ጣሪያ ከፍ በማድረግ ስራው ሲከናወን የቆዬ ቢሆንም የማስወገድ ሂደቱ በሚፈለገው ልክ እየተከናወነ ባለመሆኑ ንብረቶች ለከፍተኛ ብልሽት እና ብክነት ተጋልጠዋል።

በመሆኑም መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገቢ በወቅቱ እንዲያገኝ ለማድረግ በድጋሜ ንብረት የማስወገድ የግንዘብ ጣሪያ በመመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 31.2 የተቀመጠዉ የነጠላ ዋጋ ብር 1,000.00 /አንድ ሽህ /በታች የነበረው ተሻሽሎ ብር 3,000.00 /ሶስት ሽህ ብር/ እና ጠቅላላ ዋጋቸው በተመለከተ በደብዳቤ ቁጥር አብክመ /ገኢት/ ክቢ-01/10 በቀን 10/11/2010 ዓ/ም በተላለፈው ሰርኩላር የተቀመጠዉ የግንዘብ ጣሪያ ተነስቶ፡-

ሀ/ ክብረታ ብረት እና ተሸከርካሪ ዉጭ ያሉ ማንኛዉም የመንግስት መ/ቤት ንብረቶች በክልል መ/ቤቶች ፡በዞን፡በከተማ አስተዳድሮች ፡ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት፡የክልል ተጠሪ መ/ቤቶች እና የግሸ ንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል ያላቸዉ መ/ቤቶች ንብረቶችን የግንዘብ ጣሪያ ገደብ ሳይደረግ በንብረት አስተዳደር መመሪያ

ቁጥር 2/2003 የተደነገጉትን የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት በማድረግ በራሳቸዉ በኩል በመወሰን የማስወገድ ስልጣን እንዲኖራቸዉ ተደርጓል፡፡

ለ/ በሽያጭ ከሚወገድ ንብረት የሚገኘው ገቢ ለትሬዠሪ የሚላከዉ የሂሳብ ሪፖርት አካል ሆኖ፡-

- በወረዳ፤በዞን ፤ በከተማ አስተዳደር መ/ቤቶች ለሚገኙበት የአስተዳደር እርከን ሙሉ በሙሉ በካፒታል በጀት ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ግንባታ አገልግሎት እንዲውል ተፈቅዷል፡፡
- በክልል ደረጃ የሚገኙና የክልል ተጠሪ ተቋማት ከንብረት ማስወገድ የሚገኘዉን ገቢ ለትሬዠሪ ለሚቀርበዉ የሂሳብ ሪፖርት አካል ሆኖ ለቋሚ ዕቃ ግዥ ብቻ እንዲያዉሉ ተፈቅዷል፡፡

ሐ/ በሽያጭ የሚወገዱ ተሸከርካሪዎች ከዚህ በፊት በሥራ ላይ በነበረው አሰራር መሰረት ተፈርጀው መረጃዉ ለገንዘብ ቢሮ ቀርቦ በቢሮው በኩል እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

መ/ በቢሮዉ በኩል በሽያጭ ከሚወገዱ ተሸከርካሪዎች የሚገኘው ገቢ ለትሬዠሪ የሚላከዉ የሂሳብ ሪፖርት አካል ሆኖ፡-

- 90%ለንብረቱ ባለቤት ወረዳ፤ዞን፤ብሄረሰብ ዞን ፤ከተማ አስተዳደር ለሥራ ማስኬጃ ለቋሚ ዕቃ የሚዉል ሆኖ፤
- ቀሪዉ 10 % የሚሆነዉ ድርሻ ለገንዘብ ቢሮ (ለትሬዠሪ) ገቢ የሚደረግ ሲሆን፤
- በክልል ደረጃ ከሚገኙ መ/ቤቶች እና ከክልል ተጠሪ መ/ቤቶች የሚወገዱ ተሸከርካሪዎች የሚገኘዉ ገቢ ደግሞ ሙሉ በሙሉ (100%) ለገንዘብ ቢሮ (ትሬዠሪ) ገቢ ይደረጋል፡፡

ሠ/ የመንግስት ንብረት በሽያጭ ለማስወገድ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ በንብረት መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 39.4.1 ብር 30,000 (ሰላሳ ሽህ ብር) በላይ በሚል የተቀመጠዉ ተሻሽሎ ብር 150,000 (አንድ መቶ አምሳ ሽህ) በላይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ይህ የገንዘብ ጣሪያ ተሸከርካሪ በሽያጭ የማስወገድ ተግባር አይመለከትም፡፡

8- መመሪያዉን ስለማሻሻል ፦

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛዉም ጊዜ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡

9- መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ፦

ይህ መመሪያ ከግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ጥላሁን መሐሪ (ዶ/ር)
ቢሮ ኃላፊ
ግንቦት 2014 ዓ/ም

ባሕር ዳር